# ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የተሰጠ ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች (አክሲዮኖች) በሙሉ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን መመዝገብ እንዳለባቸው በካፒታል ገበያ አዋጅ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ተደንግጓል።

የምዝገባ ህጉ ተፈጻሚነት የሚኖረው፤

1ኛ ከዚህ ቀደም አክሲዮኖቻቸሁን ለህዝብ የሸጣችሁ፣

2ኛ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የአክሲዮን ሽያጭ ጀምራችሁ ሽያጬ አሁንም በሂደት ላይ የሆነ ወይም አዲስ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚያወጡ የአክሲዮን ማህበራት ላይ ሲሆን

በመመሪያው የሽግግር አንቀጽ መሰረት አክሲዮኖች ከዚህ ቀደም ለህዝብ ሸጣችሁ ሽያጫችሁን ያጠናቀቃችሁ እና መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ሽያጭ ጀምራችሁ እስካሁን ሽያጭ በማካሄድ ላይ ያላችሁ የአክሲዮን ማህበራት እነዚህን አክሰዮኖች ለማስመዝገብ

# ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የተሰጠ ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

በመመሪያው የተቀመጠው የአንድ አመት የሽግግር ድንጋጌ የጊዜ ገደብ ህዳር 16 ቀን 2018 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ይህ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት መመሪያው የሚጠይቀውን መስፈርት በሟሟላት አክሲዮኖቻችሁን በባለሥልጣኑ እንድታስመዘግቡ በጥብቅ እያሳሰብን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻችሁን ያላስመዘገባችሁ የአክሲዮን ማህበራት ላይ ባለስልጣኑ ህጋዊ እርምጃዎችን እንደሚወሰድ በጥብቅ ያሳስባል።

በተጨማሪም መመሪያው ከወጣ በኋላ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሽያጭ ለማቅረብ የምትፈልጉ የአክሲዮን ማህበራት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻችሁን ለሽያጭ ከማቅረባችሁ በፊት ተገቢውን መስፈርት በሟሟላት ማስመዝገብ እንዳለባችሁ በጥብቅ እናስገነዝባለን።

የምዝገባ መስፈርቶችን እና የምዝገባ ሂደቱን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 ይመልከቱ ወይም በ011-5-57-81-20 ይደውሉ።